# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት

# ማላቂያ ስትራቴጂ

መስከረም 2018ዓ.ም

ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 3

1. መግቢያ ........ 3

2. ዳራ (መነሻ ሁኔታ) ........ 4

  2.1. በተማሪ ........ 4

  2.2. በመምህር ........ 5

  2.3. በወላጅ ........ 5

3. አስቻይ ሁኔታዎች ........ 6

4. ገቺ ሁኔታዎች ........ 6

5. ዓላማ ........ 7

6. ዝርዝር ዓላማ ........ 7

7. የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ማሻሻያ ስትራቴጂዎች ........ 7

8. የስትራቴጂዎች ማስፈፀሚያ የጊዜ ሰሌዳ ........ 8

ክፍል ሁለት ........ 9

ስትራቴጂ አንድ፡ ክላስተር ማዕከላት ለTop-25 ተማሪዎች ........ 9

ስትራቴጂ ሁለት፡ የተማሪዎች የጥናት ፎረም (After-Class/ study forum) ........ 13

ስትራቴጂ ሶስት፡ Bfore class ($B_1$ እና $B_2$ class) School based tutorial/ ........ 16

  1. $B_1$-Class ቶፕ-25 የማጠናከሪያ ትምህርት ........ 16

  2. $B_2$-Class የመደበኛ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ........ 17

ስትራቴጂ አራት፡ አማካሪ መምህራንን እና ተማሪዎችን መሰየም ........ 19

ክፍል ሶስት ........ 21

አደረጃጀት እና አመራር ........ 21

  በከተማ ደረጃ ........ 21

  በክፍለ ከተማ ደረጃ ........ 22

  በክላስተር ማዕከል ደረጃ ........ 23

  በት/ቤቶች ደረጃ ........ 24

የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ የድርጊት መርሃ ግብር ........ 28

ማጠቃለያ ........ 29

አባሪዎች ........ 30

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት እና ብልፅግና መሰረት ነው፡፡ የተማረ ማህበረሰብ በሀገር ግንባታ ውስጥ የሚኖረው ሚና በጣም ከፍተኛ ነው በአንፃሩ የትምህርት ጥራት መጓደል በእያንዳንዱ የሥራ መስክ የሚፈለገውን ሥነ-ምግባር ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት እንዲከሰት የሚያደርግ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዝቅተኛ የምርት መጠን፣ ሥራ አጥነት፣ ጤናማ ትርፍ ማግኘት ቀርቶ በአቋራጭ መክበርን እንዲሁም የስራ አጦች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ለማኅበራዊ ደኅንነት ጥበቃ ከፍተኛ ወጪ ማውጣት፣ ከግብር የሚገኝ ገቢ መቀነስ በአጠቃላይ ችግሩ በጣም ብዙ ነው፡፡

የትምህርት ጥራት ሲጓደል ትምህርት/ሥልጠና የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ ስለማይችል ከፍተኛ የሆኑ ምስቅልቅሎች ይከሰታሉ፡፡ ለምሳሌ ሙስና እንዲህ ትልቅ ችግር እየሆነ የመጣው ትምህርት የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ ባለመቻሉ ነው፡፡ ወጣቱ የውጭ ባህል አራማጅ የሆነውና የተለያዩ ሱሶች ተጠቂ ለመሆንና ለወንጀል መበራከት የትምህርት ጥራት መጓደል አንዱና ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ ለእሴቶቻችን መሸርሸር ዋናው መነሻ ምክንያት የትምህርት ጥራት መጓደል ነው፡፡(ት/ት ሚኒስቴር ሪፖርት)

መንግስትም ይህንን ችግር በመረዳት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ በጀት መድቦ ዜጎቹን ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በማስተማር ላይ ይገኛል ሆኖም ግን መንግስት የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት ባለ ልክ ግን የትምህርት ጥራቱ ሊመጣ አልቻለም ለዚህም መገለጫ የሚሆነን ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታት የ12ኛ ክፍል ሀገር ሀቀፍ ፈተና የተፈተኑ ተማሪዎች ውጤት ነው፡፡ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ከተፈተኑት በ2014ዓ.ም 3.3 %፣ በ2015ዓ.ም 3.2%፣ በ2016ዓ.ም % እንዲሁም በ2017ዓ.ም በተወሰነ መልኩ መሻሻል አሳይቶ % የሚሆኑ ተማሪዎች ብቻ በሁሉም የትምህርት አይነት ከ50% በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከአገር አቀፉ የማለፍ ምጣኔ የተሻለ የተመዘገበበት ከተማ አስተዳደር ቢሆንም የየዓመቱን ውጤት ማየት ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተና ከተፈተኑ ተማሪዎች በ2014ዓ.ም 19.78%፣ በ2015ዓ.ም 16.16%፣ በ2016ዓ.ም 21.35% እንዲሁም በ2017ዓ.ም መሻሻል አሳይቶ 31% የሚሆኑ ተማሪዎች ብቻ በሁሉም የትምህርት አይነት ከ50% በላይ ውጤት አስመዝግበው ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት ችለዋል፡፡ (አ/አ ት/ት ቢሮ ሪፖርት

## 2. ዳራ (መነሻ ሁኔታ)

### የ2014-2017ዓ.ም የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ውጤት እንደመነሻ

| | | የተመዘገቡ | | | ≥50/100 | | | በፐርሰንት | ለውጥ | ከፍተኛ ውጤት ያመጡ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | | | |
| 2014ዓ.ም | ተፈ.ሳይንስ | 12242 | 13061 | 25303 | 3652 | 3431 | 7083 | 27.99 | | 117 |
| | ማህ.ሳይንስ | 9028 | 13648 | 22676 | 1081 | 1327 | 2408 | 10.62 | | 8 |
| | ድምር | 21270 | 26709 | 47979 | 4733 | 4758 | 9491 | 19.78 | +0.26 % | 125 |
| 2015ዓ.ም | ተፈ.ሳይንስ | 13892 | 14847 | 28739 | 3079 | 2984 | 6063 | 21.10 | | 97 |
| | ማህ.ሳይንስ | 9445 | 15329 | 24774 | 1071 | 1394 | 2465 | 9.95 | | 6 |
| | ድምር | 23337 | 30176 | 53513 | 4150 | 4378 | 8528 | 15.94 | -3.84% | 103 |
| 2016ዓ.ም | ተፈ.ሳይንስ | 12739 | 14021 | 26760 | 3874 | 3718 | 7592 | 28.37 | | 451 |
| | ማህ.ሳይንስ | 8842 | 14467 | 23309 | 1370 | 1728 | 3098 | 13.29 | | 24 |
| | ድምር | 21581 | 28488 | 50069 | 5244 | 5446 | 10690 | 21.35 | +5.41 % | 475 |
| 2017ዓ.ም | ተፈ.ሳይንስ | 12142 | 13648 | 25790 | 5085 | 5379 | 10464 | 40.57 | | 1250 |
| | ማህ.ሳይንስ | 9573 | 15228 | 24801 | 2247 | 2963 | 5210 | 21.01 | | 71 |
| | ድምር | 21715 | 28876 | 50591 | 7332 | 8342 | 15674 | 30.98 | +9.6 % | 1321 |
| 2014-2017ዓ. | ተፈ.ሳይንስ | 51015 | 55577 | 106592 | 15690 | 15512 | 31202 | 29.27 | | 1915 |
| | ማህ.ሳይንስ | 36888 | 58672 | 95560 | 5769 | 7412 | 13181 | 13.79 | | 109 |
| | ድምር | 87903 | 114249 | 202152 | 21459 | 22924 | 44383 | 21.96 | +11.2% | 2024 |
| 2018ዓ.ም | ተፈ.ሳይንስ | | | | | | | | | |
| | ማህ.ሳይንስ | | | | | | | | | |
| | ድምር | | | | | | | 60 % | +19 % | |

### 2.1. በተማሪ

**በጥንካሬ**

- ከላይ በሰንጠረዥ በተቀመጠው ልክ የተማሪዎች ውጤት ከዓመት ዓመት መሻሻል ማሳየቱ
- የተማሪዎች ወደ ዩንቨርስቲ የመግቢያ ምጣኔ እያደገ በመምጣቱ የተማሪዎች መማር ተነሳሽነት መኖሩ
- ተማሪዎች ቴክኖሎጅዎችን ለመማር የመጠቀም እድል መኖር
- አብዛኛዉ ተማሪዎች የሥነ መግባር ማሻሻል ማሳየታቸው

**መሻሻል የሚገባው**

- የተማሪዎች ሶሻል ሚድያን ያለአግባብ መጠቀም ( ለሶሻል ሚድያ ሱሰኝነት መጋለጥ ፣መኖሩ)
- ለመማር ማስተማር አስፈላጊ ግብዓት አሟልቶ ትምህርት ቤት አለመገኘት( መጸሀፍ፣ደብተር..)

- መቅረትና ማርፈድ መኖር
- በበዓላት ሰሞን ከትምህርት ገበታ መቅረት
- አብዛኛው ተማሪ በማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራም አለመገኘት
- አንዳንድ ተማሪዎች ለመምህራኖቻቸው አክብሮት አለመስጠትና አለመታዘዝ
- ቤተ መጻህፍት የመጠቀም ዝንባሌ አለመኖር
- የትምህርትን ጥቅም አለመረዳትና ፍላጎት ማጣት

## 2.2. በመምህር

**በጥንካሬ**

- ✓ የቅዳሜ ትምህርት/ማጠናከሪያ መስጠት መቻል
- ✓ የተለያዩ ዎርክሺቶችን በተደጋጋሚ የሚያሰሩ መምህራን መኖራቸው
- ✓ በተሰወነ መልኩ የፈተና ቢጋር በአግባቡ የሚጠቀሙ መምህራን መኖራቸው
- ✓ ጥቂት መምህራን ለተማሪዎች ለውጥ የሚለፉ መኖራቸው
- ✓ ወስን መምህራን ይዘታቸውን ባቀዱት መልኩ የሚተገብሩ መሆናቸው

**መሻሻል የሚገባው**

- ➢ የመምህራን ዝግጅት ለሀገር አቀፍ ፈተና ከማዘጋጀት አኳያ የተቃኘ አለመሆን
- ➢ ክፍለ ጊዜ መሸራረፍ እና ማባከን የሚስተዋል መሆኑ
- ➢ በጥናትና ምርምር በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ክፍተቶች የሞሉ ያለመሂድ
- ➢ ተከታታይ ሙያ ማሻሻያን ተግባራዊ በማድረግ ራሳቸውን ያለማሻሻል ክፍተት
- ➢ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ እውቀትና አጠቃቀም ክፍተት መኖር
- ➢ የምዘና ሂደታቸው ሳይንሳዊ ያለመሆኑ እና በደንብ ያልተቃኘ መሆኑ
- ➢ ተማሪዎች ቤተ መጽሃፍት ገብተው እንዲያነቡ የማድረግ ልማድ ያለመኖር
- ➢ መምህራንን ቤተ መጽሃፍት በመጠቀም እውቀት እና ክህሎታቸውን የማሳደግ ክፍተት

## 2.3. በወላጅ

**በጥንካሬ**

- ❖ የተወሰኑ ወላጆች ተማሪዎች የማጠናከር  ትምህርት እንዲማሩ ማድረግ እንዲሁም አስፈላጊዉን ትብብር ማድረግ

**መሻሻል የሚገባው**

- ወላጆች ከትምህርት ቤት ጋር የተሻለ ግኙኝነት አለመኖሩ
- ለልጆቻቸው የሚሰጠዉን ትምህርት በተለየ መልኩ /በተሻለ መንገድ አለመከታተል (የሚሰጡ ማጠናከርያ ትምህርት፤ የፈተናዎቻቸዉን ዉጤታቸዉን አለመከታተል
- በልጆቻቸዉ ዙሪያ ያደረጉትን የአራትዮሽ ውል ስምምነት ተግባራዊ አለመደረጉ
- በልጆቻቸዉ ዉጤት ዙሪያ ከሚመለከተዉ አካላት ወቅቱን ጠብቆ ዉይይት እና ክትትል አለመደረግ

## 3. አስቻይ ሁኔታዎች

1. መንግስት ብሎም የከተማ አስተዳደሩ ትምህርት ቢሮ የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ የሰጠው ትኩረት
2. ከ2014ዓ.ም - በ2017ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና የተፈተኑ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት አይነት ከ50% ባላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከዓመት ዓመት መሻሻል ማሳየቱ (ዝቅተኛ ቢሆንም)
3. በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት አመራሮች የ12ኛ ክፍል የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ያላቸው ቁርጠኝነት
4. ትንሽ ድጋፍ ካገኝ ውጤቱን ለማሻሻል ብቁ ንቁ እና ዝግጁ ተማሪ መኖሩ
5. መምህራን እና የትምህርቱ ማህበረሰብ ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው ተማሪዎቻቸውን ለማብቃት ዝግጁ መሆናቸው
6. ወላጆች ለልጆቻቸው ውጤት መሻሻል ወደኋላ የሚሉት ጉዳይ የሌላቸው መሆኑ፡፡
7. በትምህርት ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት አሳማኝ ፕሮፖዛል ከቀረበላቸው ተማሪዎችን ለማገዝ ፍቃደኛ መሆናቸው

## 4. ገቺ ሁኔታዎች

1. በውስን አካላት የሚስተዋል ቸልተኝነት እና ቁርጠኝነት ማነስ
2. አንዳንድ መምህራን እና ተማሪዎች ዓላማውን በደንብ ባለመረዳት ትኩረት ማነስ
3. በዘልማድ ስራዎችን የመስራት ሁኔታ ማለት እንደተለመደው የማጠናከሪያ ትምህርት ለመስጠት መሞከር
4. አንዳንድ አመራሮች የፕሮጀክቱን ጠቀሜታ ባለመረዳት የትኩረት ማነስ
5. የሃላፊዎች መቀያየር
6. ወላጆች በጥቃቅን ሰበብ የልጆቻቸውን ውጤት ማሻሻያ እቅድ ሙሉ ለሙሉ አለመፈፀም

## 5. ዓላማ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን ውጤት ማሻሻያ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ በመተግባር እና የመማማር ባህል በመገንባት በ12ኛ ክፍል ተማሪዎቻችን የላቀ አገር አቀፍ ፈተና ውጤት የሚመዘን የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ፡፡

## 6. ዝርዝር ዓላማ

- በ2017 የትምህርት ዘመን 50 ከመቶ እና በላይ ያመጡ ተማሪዎችን ቁጥር ከ31% ወደ 60% ማድረስ
- የተማሪዎችን የመማር እና የመማማር ባህል ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ
- የሥነ-ትምህርት ሳይንስን የተከተለ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበልን መሰረት ያደረገ የትምህርት ውጤት ማሻሻያ ስረዓት ማስፈን

## 7. የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ማሻሻያ ስትራቴጂዎች

I. ክላስተር ማዕከላት ለTop-25 ተማሪዎች

II. After-class /የጥናት ፎረም/study forum

III. Before-class /School based tutorial

IV. የአማካሪ መምህራን-ተማሪ ምደባ

# 8. የስትራቴጂዎች ማስፈፀሚያ የጊዜ ሰሌዳ

| | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ1፡00-2፡00 | B-class $B_1$ School based $B_2$ Top-25 | | B-class $B_1$ School based $B_2$ Top-25 | | B-class $B_1$ School based $B_2$ Top-25 | | |
| ከ2፡30-6፡30 | | | | | | ➤ Cluster tutor<br>School based | |
| ከ7፡30-9፡00 | | | | | | ➤ Cluster tutor<br>School based | |
| ከ9፡30-12፡00 | | A-class<br>➡ Study forum | | A-class<br>➡ Study forum | | | |

ተማሪዎችን ለማጠናከር የማጠናከሪያ ትምህርት የሚሰጥበት ጊዜ

1. B-class (ከመደበኛ ክፍል በፊት ከ1፡00-2፡15) 1ሰዓት
2. A-class (ከመደበኛ ክፍል በኋላ) 2ሰዓት
3. ቅዳሜ 6 ሰዓት

ቶፕ ተማሪዎች

- በሳምንት ለ9 ሰዓት ይማራሉ
- በሳምንት 2 ሰዓታት ይማማራሉ

መካከለኛ ተማሪዎች

- 9 ሰዓት ይማራሉ
- በሳምንት 2 ሰዓታት ይማማራሉ

የማጠናከሪያ ትምህርቱ ዓይነት

1. School based (መካከለኛ ተማሪዎች) ይማራሉ
2. Study forum (ከጓደኞቻቸው ይማማራሉ)
3. Cluster tutor (ለቶፕ-25) (ይማራሉ)

# ክፍል ሁለት

## ስትራቴጂ አንድ፡ ክላስተር ማዕከላት ለTop-25 ተማሪዎች

በክላስተር ማእከል የሚሰጥ የማጠናከሪያ ትምህርት ማለት ጂኦግራፊካሊ ተቀራራቢ የሆኑ የግልና የመንግስት ት/ቤት የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል Top-25 ተማሪዎችን አቀናጅቶ በክላስተር ማዕከል የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት በአገር አቀፍ ፈተና ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ለማስቻል የሚሰራበት መዋቅር ነው

**አላማ**

- በየት/ቤቱ ያሉ Top-25 ተማሪዎችን ሙሉ ለሙሉ ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ ወደ ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ ማስቻል
- በተማሪዎች መካከል ተቀራርቦ በጋራ የመማር ባህል ለመገንባት (cooperative learing)
- ተማሪዎች በአዎንታዊ የውድድር ስልት የመማር ሁኔታ ለመፍጠር
- የተማሪዎችን የላቀ ውጤት የማምጣት ስነ ልቦና መገንባት
- ተማሪዎች በዋና ዋና የትምህርት አይነቶች ላይ ያላቸውን የክህሎት እና የእውቀት ደረጃ ማሻሻል
- ተማሪዎች ግብ ጥለው በተሳካ ሁኔታ ለብሄራዊ እና ለክፍል ፈተናዎች ዝግጁ እንዲሆኑ ማብቃት
- የተማሪዎችን ችግር የመፍታት፣ የመግባባት እና ለጋራ ውጤት በህብረት የመስራት ክህሎታቸውን ማጎልበት
- የተሻለ ብቃት እና አቅም ባላቸው መምህራን ጥራት ያለው ት/ት ለመስጠት እና ለተሻለ ውጤት ለማብቃት

**ግብ 1 የክላስተር ማዕከል ማዋቀር**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- መሰረተ ልማቱ የተሟላ፣ ለአጎራባች ትቤቶች አማካይ ርቀት ላይ የሚገኝ፣ ለተማሪ ምቹ የሆነ ት/ቤትን ለክላስተር ማዕከልነት መለየት
- የክላስተር ማዕከሉን ር/መምህራን በአስተባባሪነት ኃላፊነት መስጠት
- በመስፈርት የተመለመሉ መምህራንን መመደብ
- ከየት/ቤቱ የተለዩ Top-25 ተማሪዎችን ዝርዝር መረከብ

- የክፍል-ተማሪ፣ የክፍል-መምህር ድልድል መስራት
- የማጠናከሪያ ትምህርቱን የፋይናንስ ስረዓት መዘርጋት

**ዝርዝር ተግባራት**

- ሁሉም ክ/ከተማው ስር የሚገኙ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን በክላስተር ማደራጀት
- የክላስተር ማእከል ሆኖ የተመረጠውን ት/ቤት ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ
- በየት/ቤቱ ከወላጅ እና ከተማሪ ጋር በመርሃ ግብሩ ውይይት ማድረግ
- ከTOP-25 ተማሪ ወላጆች ጋር በመግባባት በወር 300 ብር ማሰባሰብ
- የተሰበሰበውን ፋይናንስ በክላተር ማዕከሉ በጋራ በሚከፈት አካውንት ገቢ ማድረግ
- ት/ቢሮ በሚያስቀምጠው የክፍያ ስርዓት መሰረት ለመምህራን እና ለሚመለከታቸው አካላት ክፍያ መፈጸም
- የክላስተሩ አስተባባሪው በክላስተር ማእከሉ ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታን ይፈጥራል
- የክላስተሩ አስተባባሪው ከየት/ቤቱ የመጡትን ተማሪዎች ወደ አንድ ቋት በማስገባት መቀላቀል እና መመደብ

**ግብ 2 የክላስተር** Top-25 **ማጠናከሪያ ትምህርት ተሳታፊ ተማሪዎችን መለየት**

ዋና ተግባር

- በክላስተር ማዕከል የሚማሩ ተማሪዎች ሙሉ ለሙሉ በአገር አቀፍ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ሊያስመዘግቡ መለየታቸውን ግንዛቤ መፍጠር
- በ2017 ከየክፍላቸው ከ1ኛ እስከ 25ኛ የወጡ የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን መለየት
- የተመረጡ ተማሪዎችን ዝርዝር ለክላስተሩ በመላክ እና ለተማሪዎቹም መመደባቸውን ማሳወቅ

ዝርዝር ተግባር

- ለተመረጡ ተማሪዎች በት/ቤት ደረጃ የግንዛቤ መድረክ መፍጠር
- በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪ ወላጆችን በማሳወቅ በሂደቱ ፣ በክፍያ እና ተያያዥ ጉዳዮች የጋራ መግባባት ላይ መድረስ
- ተማሪዎች የራሳቸውን ግብ እንዲጥሉ ይደረጋል
- ውጤታቸውን ያሻሻሉ የፕሮግራሙን መስፈርት የሚያሙዋሉ ተማሪዎችን ማካተት

**ግብ 3 የመምህራን ምልመላ ማካሄድ**

ዋና ተግባር

- ❖ በከተማ ደረጃ የመምህራንን ምልመላ መስፈርት ማዘጋጀት

- ❖ የማጠናከሪያ ትምህርት የሚያስተምሩ መምህራንን በመስፈርት መሰረት መለየት
- ❖ ለተመረጡ መምህራን የአሰራር ሂደቱን በተመለከተ ግንዛቤ መስጠት

ዝርዝር ተግባር

- ለተመረጡ መምህራን የተዘጋጀውን የጥናት ይዘት ማስተዋወቅ
- በተዘጋጀው ይዘት መሰረት አመታዊ እቅድ እንዲያዘጋጁ ማድረግ
- ከጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ጋር ለተግባራዊነቱ የጋራ ውል ማስገባት

**ግብ 4 የክላተር ማጠናከሪያ ትምህርት ፕሮግራም አተገባበር መምራት**

**ዋና ተግባር**

- በክላስተር ደረጃ የሚከናወነውን የጥናት ፕሮግራም ማዘጋጀት
- የክላስተር ማዕከሉ ት/ቤት ዋና እና ምክትል ር/መምህራን ሙሉ ሂደቱን እንዲመሩ ሩላፊነት ከተጠያቂነት ጋር መስጠት
- የተማሪዎችን የምዘና ጊዜ ያካተተ ፕሮራም በክላስተር ደረጃ ማዘጋጀት

**ዝርዝር ተግባር**

- የጥናት ፕሮግራሙን ለጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ፤ የተማሪ ወላጆች እና መምህራን ማሳወቅ
- አመታዊ የተከታታይ ምዘና ፕሮግራሙን ለተማሪዎች ማሳወቅ
- የጥናት እና የምዘና ጊዜ አተገባበሩን ክትትል ማድረግ
- የመለማመጃ ጥያቄ ዘወትር በየሳምንቱ የተማሩትን መሰረት ባደረገ መልኩ ማዘጋጀት
- ሞዴል ፈተናዎችን የዩንቨርሲቲ መግቢያ ፈተና በሚዘጋጅበት መንገድ በቢጋር ተዘጋጅተው ለተማሪዎች በ 2 ወር አንድ ግዜ መስጠት
- ለዋናው ፈተና ዝግጅት ይረዳቸው ዘንድ ኦንላይን ፈተና በአመት 2 ጊዜ በማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅታችውን እንዲያጠናክሩ ማድረግ

**ግብ 5 ጥሩ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች እና መምህራን እውቅና መስጠት**

**ዋና ተግባር**

- የሚሰጡ ምዘናዎችን በመተንተን የተማሪዎችን አሁናዊ ሁኔታ ምገምገም
- የመምህራኑን የስራ አፈጻጸም በየወቅቱ በመገምገም መረጃ መያዝ
- ተከታታይ ምዘናዎች ወቅቱን ጠብቀው ውጤት ማስፈርያ ላይ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለተማሪዎች ወቅታዊ ብቃታችውን መሰረት ያደረገ ሽልማት በሴሚስተር አንድ ግዜ መስጠት
- በክላስተር ማእከል አጥንተው በሃገር አቀፍ ፈተና ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡትን ተማሪዎች እውቅና መስጠት
- ከግባቸው አንፃር 100% ያሳኩትን ተማሪዎች እውቅና መስጠት
- የክፍለ ግዜ ብክነት እንዳያጋጥም በሚቀሩ መምህራን ሌሎች መምህራን ተተክተው እንዲሸፍኑ በማድረግ ለሸፈኑት ክፍለ ግዜ የክፍለ ግዜዉን ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ

**ግብ 6 ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪ ወላጆች ጋር በጋራ መስራት**

**ዋና ተግባር**

- በክላስተር ማዕከላት የማጠናከሪያ ትምህርቱን ዓላማ ለወላጆች ማስገንዘብ
- ወላጆች የፋይናንስ ምንጭ በመሆኑ ለስራው ስኬት ሚናቸውን እንዲወጡ መምራት
- ከተማሪዎች ወላጆች ጋር በየመጡበት ት/ቤት በወር መጨረሻ የጋራ መድረክ በማዘጋጀት በመማር ማስተማር ሂደቱ እና በልጆች ለውጥ ላይ ምክክር ማካሄድ
- በመድረክ የሚነሱ ሃሳብ አስተያየቶችን በመውሰድ ለለውጥ መስራት

**ዝርዝር ተግባር**

- የስብሰባ ጥሪዎችን በደብዳቤ ለተማሪዎች ወላጆች አስቀድሞ ማሳወቅ
- ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ የመረጃ ለውውጥ ዘዴ በመጠቀም ወቅታዊ የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ ማካሄድ
- ከወላጆች የሚነሱ ሀሳቦችን በመውሰድ ከመምህራን ጋር ውይይት ማከናወን
- ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርት አቀባበል ለውጥ የሚገመግሙበትን መጠይቅ ማዘጋጀ

**ግብ 7 በክላስተር ማዕከል የሚሰጥ ማጠናከሪያ ትምህርት ፋይናንስ**

**ዋና ተግባር**

- በክላስተር ማዕከል አስተባባሪዎች ማለትም ር/መምህር፣ ሱፐርቫይዘር እና የማዕከሉ ወተመህ ሰብሳቢ ሆነው በጋራ አካውንት ይከፈታል
- የተማሪ ወላጆች ክፍያ በአካውንቱ ማስገባታቸውን የየት/ቤቱ ር/መምህር ይከታተላል
- በክላስተር ለሚያስተምሩ መምህራን ፣ ለሚያስተባብሩ ር/መምህራን፣ ሱፐርቫይዘር፣ ለየት/ቤቱ ዋና ር/መምህር ክፍያ በሚቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ይፈፀማል

## ስትራቴጂ ሁለት፡ የተማሪዎች የጥናት ፎረም (After-Class/ study forum)

የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል መሰረት አድርጎ (ሁሉንም የተማሪ ዓይነት ያካተተ) ከ3-7 ተማሪዎች ያሉትና ከመምህራን ተመርጠው የሚሰጡ ሌሰኖችን እና ጥያቄዎችን በተናጥል ቀጥሎም በቡድን በመስራት በክፍል ውስጥ እና ውጪ ተማሪዎች በመደጋገፍ ውጤት እና ሥነ-ምግባራቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ አደረጃጀት ነው፡፡

ዓላማ፦

- የተማሪዎችን በግል እና በጋራ የመስራት ባህል መገንባት (cooperative learing)
- በተማሪዎች መካከል የተሻለ ትብብር እና መደጋገፍ በመፍጠር ለብሔራዊ ፈተና ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል፤
- ተማሪዎች እውቀታቸውን፣ ልምዳቸውን እና የአጠናን ዘዴአቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲያጋሩ ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤
- የተማሪዎችን የማንበብ ባህል፣ ልምድና ክህሎት ማሳደግ፤
- የተማሪዎችን የመማር እና የመፈተን አቅም ማሳደግ፤

**ግብ 1. የጥናት ፎረም ማደራጀት**

**ዋና ተግባር**

- የተማሪዎችን ውጤት እና ጾታዊ ስብጥር ጠብቆ በጥናት ፎረም ማደራጀት
- ለጥናት ፎረም አስተባባሪ አካል ኃላፊነት መስጠት
- በጥናት ፎረሙ ዓላማ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በት/ቤቶች የጥናት ፎረም ማስጀመር

**ዝርዝር ተግባራት**

- በትምህርት ቤቱ የት/ቤት መሻሻል ምክትል ር/መ/ር እንዲመራ ማድረግ፤
- ለመምህራን ለተማሪዎች እና ለወላጆች መድረክ ፈጥሮ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ተማሪዎችን በ2017 ዓ.ም ውጤት መነሻ በማድረግ በደረጃቸው እና በመማር ብቃታቸው /ፈጣን፣ መካከለኛ እና መጠነኛ / በማለት መለየት እና አመጣጥኖ ማደራጀት
- የአንድ የጥናት ፎረም አባል ብዛት ከ7 ተማሪዎች ያልበለጠ እንዲሆን በማድረግ ማደራጀት፤
- የክፍል ሃላፊ መምህራን በክፍል ደረጃ ያለወን የጥናት ፎረም ያስተባብራል

- በየክፍሉ የተደራጀውን የጥናት ፎረም  አረጋግጦ ማፅደቅ፤
- በትምህርት አይነቱ የተለያዩ ጥያቄዎች (ወርክሽት) የሚያዘጋጅ ቲም ማደራጀት

**ግብ 2. የጥናት ፎረሙን ማካሄድ**

**ዋና ተግባር**

- ጥናቱ የሚካሄድበትን ክፍል ማመቻቸት
- የሚጠኑ የትምህርት ዓይነቶችን መለየት
- መርክ ሽት እና ወርክ ቡክ ማዘጋጀት
- ፕሮግራም አዘጋጅቶ መተግበር

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለመምህራን፤ ለተማሪዎች እና ወላጆች ግንዛቤ መፍጠር፤
- የተዘጋጀውን ወርክሽት ለተማሪዎች እንዲደርስ በማድረግ ፤በግል እና በቡድን መስራታቸውን መከታተል
- በጥናት ፎረሙ በተናጥል ወይንም  በቡድን  እንዲያነቡ ማድረግ፤
- የጥናት ፎረሙ በተቀመጠለት  የግዜ ሰሌዳ /ማክሰኞ እና ሐሙስ/ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ማድረግ፤
- አጠቃላይ የጥናት ፎረሙን አተገባበርና ውጤታማነት በየደረጃው ያለው የትምህርት አመራር እና ባለሙያ ክትትል ፤ድጋፍ እና የግብረ-መልስ ማካሄድ፤
- ሂደቱን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገምገም መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች እያሻሻሉ መሄድ፤
- የተለያዩ መጽሃፍትን፣ ያለፉ ፈተናዎችን፣ ማስታዎሻዎችን፣ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በጋራ እንዲጠቀሙ ማስቻል፤ ቤተመጽሃፍት እንዲሄዱ መምህራን ከቤተ መጽሃፍት ጋር ቁርኝት ያላቸውን የቤት ስራዎችን አዘውትረው እንዲሰጡ ማበረታታት፤

**ግብ 3. የጥናት ፎረሙ አሰራር**

**ዋና ተግባር**

- ከወርክ ሽት ወደ ወርክ ቡክ
- በግል ቀጥሎም በጋራ መማር
- በመማር ለውጥ ላይ ግብረ መልስ መስጠት

**ዝርዝር ተግባራት**

- ለእያንዳንዱ የጥናት ፎረም ቡድን ወርክ ቡክ በማዘጋጀት ተደራሽ ማድረግ፤

- ተማሪዎች በሰዓታቸው የጥናት ፎረማቸው ላይ ከተገኙ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ በግልጥያቄ ይሰራል፣ በግል የሰሩትን በጋራ ያረጋግጣሉ፤ወርክ ቡካቸውን አስረክበው የዕለቱ ጥናት ይጠናቀቃል፤
- የጥናት ቡድኑ በወርክ ቡክ የሰሩትን ጥያቄ በየትምህርት አይነቱ መምህራን ያርማል /ግብረ መልስ ይሰጣል፤
- አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በፎረሙ የሚሰራ ጥያቄ ገቢ ይደረጋል፤

**ከጥናት ፎረም የሚጠበቅ ውጤት**

- የተማሪዎች የማንበብ ባህል ይጎለብታል፤
- የተማሪዎች በግል እና በቡድን የማንበብ እና የመስራት ባህል ይዳብራል፤
- የተማሪዎችን የመማር እና የመፈተን አቅም ያሳድጋል፤
- የተማሪዎችን በራስ የመተማመን አቅም ያሳድጋል፤
- የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል፤

## ስትራቴጂ ሶስት፡ Bfore class ($B_1$ እና $B_2$ class) School based tutorial/

ከመደበኛ ክፍለ ጊዜ በፊት ዘወትር ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ ተማሪዎችን በትምህርት አቀባበላቸው እና በውጤታቸው ተለይተው በትምህር ቤት ደረጃ የሚሰጥ /school based tutorial/ የማጠናከሪያ ትምህርት ነው፡፡

**ዓላማ**

ይህ የጥናት ዓይነት ዋና ዓላማ ለፈጣን እና መካከለኛ ተማሪዎች በተለያየ ክፍል የሚሰጥ የማጠናከሪያ ትምህርት ሲሆን ፈጣኖች ወደ ላቀ መካከለኞቹን ወደ ከፍተኛ ውጤት ለማድረስ የሚሰጥ የማለዳ ትምህርት ነው፡፡

**ይህ መርሀግብር የሚከናወነው በሁለት መንገድ ሲሆን፡-**

1. Top-25 የማጠናከሪያ ትምህርት (ሰኞ ፣ረቡዕ እና አርብ ሰኞ ከ100፡2፡15)
2. የመደበኛ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት (ሰኞ ፣ረቡዕ እና አርብ ከ1፡00-2፡15፣ ቅዳሜ ሙሉ ቀን ለ6 ሰዓታት የሚከናወን ይሆናል)

**ዝርዝር አፈፃፀም**

### 1. $B_1$-Class ቶፕ-25 የማጠናከሪያ ትምህርት

ተሳታፊ፡ የ11ኛ እና 12ኛ የየክፍሉ Top-25 ተማሪዎች

ቅዳሜ ከት/ቤት ውጪ በተከፈተው ክላስተር ማዕከል የሚማሩ ይሆናሉ

ቦታ፡ ከመደበኛ መማሪያ ክፍል ወጥተው ለTop-25 ተማሪዎች በተዘጋጀ የመማሪያ ክፍል

ቀን፡ ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ

ሰዓት፡ ከ 1፡00 — 2፡15

**ግብ 1. ተሳታፊ ተማሪዎችን መለየት**

ዝርዝር ተግባራት

- በ2017ዓ.ም ውጤታቸው በየክፍሉ Top-25 ተማሪዎችን መረጃ ማደራጀት
- የማጠናከሪያ ትምህርቱን ዓላማ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ተማሪ-ክፍል ድልድል መስራት

**ግብ 2. ተሳታፊ መምህራንን በመለየት የማጠናከሪያ ትምህርት ማስጀመር**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ከ11ኛ እና 12ኛ ክፍል መምህራን በመስፈርቱ መሰረት ምልመላ ማካሄድ
- ብቁ እና ንቁ ሆነው ለተመረጡ መምህራን ግንዛቤ ማስጨበጥ

- ስራ ማስጀመር

**ግብ 3. B1-Class (Top-25 የማጠናከሪያ ትምህርት) ተማሪዎችን ማጠናከሪያ ትምህርት ማስኬድ**

ዝርዝር ተግባራት

- ለተማሪ፣ ለወላጅ፣ ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል መምህራን ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በጥብቅ ዲሲፒሊን የማጠናከሪያ ትምህርቱን ማካሄድ
- የሚያጋጥሙ የሥራ ላይ ችግርን በት/ቤት አቅም እየፈቱ ለለውጥ መስራት

**ግብ 4. ክትትል እና ድጋፍ ማስኬድ**

ዝርዝር ተግባራት

- ክፍተትን ሊሞላ የሚችል ቼክ ሊስት ማዘጋጀት
- ድጋፍ እና ክትትል ለሚያደርጉ አመራሮች እና ሱፐርቫይዘሮች ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በክትትል እና ድጋፉ የሚገኙ ግኝቶችን መገምገም
- የክፍለ ጊዜ ብክነትን በጥብቅ ዲሲፒሊን መቆጣጠር አፋጣኝ እርምት እርምጃ መውሰድ

## 2. B2-Class የመደበኛ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት

ተሳታፊ፡ የ11ኛ እና 12ኛ ተማሪዎች

ቦታ፡ በመደበኛ መማሪያ ክፍላቸው

ቀን፡ ሰኞ፣ ረቡዕ እና ዓርብ (ከጠዋቱ 1፡00-2፡15)

ቅዳሜ ሙሉ ቀን (ከ2፡30-10፡00)

**ግብ 1. ተሳታፊ ተማሪዎችን መለየት**

ዝርዝር ተግባራት

- የየክፍሉን ተማሪዎች መረጃ ማደራጀት
- የማጠናከሪያ ትምህርቱን ዓላማ ግንዛቤ ማስጨበጥ
- አስገዳጅ በሆነ መልኩ የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲገቡ ማድረግ

**ግብ 2. ለተሳታፊ መምህራ ድልድል በማሳወቅ የማጠናከሪያ ትምህርት ማስጀመር**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ከ11ኛ እና 12ኛ ክፍል መደበኛ መምህራንን ፕሮግራም ማሳወቅ
- ለመምህራን ግንዛቤ ማስጨበጥ
- ስራ ማስጀመር

**ግብ 3. $B_2$-Class የመደበኛ ተማሪዎችን ማጠናከሪያ ትምህርት ማስኬድ**

ዝርዝር ተግባራት

- ለተማሪ፣ ለወላጅ፣ ለ11ኛ እና 12ኛ ክፍል መምህራን ግንዣቤ ማስጨበጥ
- በጥብቅ ዲሲፒሊን የማጠናከሪያ ትምህርቱን ማካሄድ
- የሚያጋጥሙ የሥራ ላይ ችግርን በት/ቤት አቅም እየፈቱ ለለውጥ መስራት

**ግብ 4. ክትትል እና ድጋፍ ማስኬድ**

**ዝርዝር ተግባራት**

- ክፍተትን ሊሞላ የሚችል ቼክ ሊስት ማዘጋጀት
- ድጋፍ እና ክትትል ለሚያደርጉ አመራሮች እና ሱፐርቫይዘሮች ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በክትትል እና ድጋፉ የሚገኙ ግኝቶችን መገምገም
- የክፍለ ጊዜ ብክነትን በጥብቅ ዲሲፒሊን መቆጣጠር አፋጣኝ እርምት እርምጃ መውሰድ

## ስትራቴጂ አራት፡ አማካሪ መምህራንን እና ተማሪዎችን መሰየም

ይህ ስትራቴጂ በት/ቤቱ ያሉ ንቁ እና ብቁ መምህራንን እና የ12ኛ ክፍል ጎበዝ ተማሪዎችን ለይቶ ለተማሪዎች በመመደብ አማካሪ መምህሩ/ተማሪው ያለውን /ያላትን አቅም እና ልምድ በመጠቀም ተማሪዎችን በውጤትና ስነ-ምግባር በማነጽ ለሀገር አቀፍ ፈተና የሚያዘጋጅ/የምታዘጋጅ

**ግብ 1፡-ለተማሪዎች አማካሪ መምህራን እና አማካሪ ተማሪ እንዲመደብ ማድረግ**

**ዋና ተግባር**

- አማካሪ የሚሆኑ የት/ቤቱን መምህራን በመስፈርት መለየት
- አማካሪ የሚሆኑ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በመስፈርት መለየት
- ለአማካሪ በተመለመሉ መምህራን እና ተማሪዎች የሚሰሩ ተግባራትን መለየት

**ዝርዝር ተግባራት**

- በተማሪዎች ተቀባይነት ያላቸውን አማካሪ መምህራን እና አማካሪ ተማሪዎችን መረጃ መሰረት በማድረግ መለየት
- ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች አማካሪ የሚሆኑትን ቶፕ-25 መለየት
- ለተለዩ አማካሪ መምህራን እና አማካሪ ተማሪዎች በጋራ ውይይት ማድረግና በዓላማው ላይ መግባባት መፍጠር
- ለአማካሪዎች ሀላፊነታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ መስጠት
- በአማካሪዎች የሚሰሩ ተግባራትን በዝርዝር በማውጣት መስጠት
- አማካሪ መምህራንን ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች መስጠት
- አማካሪ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መስጠት

**ግብ 2፡-ተማሪዎችን ለአማካሪ መምህራን እና አማካሪ ተማሪዎችን መደልደል**

**ዋና ተግባር**

- ተማሪዎችን መደልደል

**ዝርዝር ተግባራት**

- የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በውጤት፣ በፆታ እና በስነ ምግባር ስብጥራቸው ከ4-7 ተማሪዎችን ማደራጀት
- ለአንድ መምህር ከ4-7 ተማሪዎችን የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ መመደብ

- ለአማካሪ ለተደለደሉ ተማሪዎች የውይይት መድረክ ማዘጋጀትና በአላማው ዙሪያ ውይይት ማድረግ
- ለአንድ 12ኛ ክፍል ኀበዝ ተማሪ 2 ተማሪዎችን መደልደል
- ከወላጆች ጋር በትስስር መስራት

**ግብ3፡- የማማከር ሂደቱን ውጤታማት መገምገም**

**ዋና ተግባር**

- የአማካሪ መምህራን አሰራር መከታተል
- የተመካሪ ተማሪዎችን ተሳትፎ መገምገም

**ዝርዝር ተግባራት**

- አማካሪ መምህራን የተመደቡላቸውን ተማሪዎች በትክክል ማማከራቸውን በድጋፍና ክትትል ማረጋገጥ
- ተማካሪ ተማሪዎች በትክክል እየተሳተፉ መሆኑን በድጋፍና ክትትል ማረጋገጥ

**ግብ 4፡- የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት**

**ዋና ተግባር**

- አማካሪ መምህራንን እና አማካሪ ተማሪዎን ማበረታታት
- ተማሪዎችን ማበረታታት

**ዝርዝር ተግባራት**

- አማካሪ መምህራን እንዲያማክሩ ከተመደበላቸው ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት 50 እና በላይ ባመጡት የተማሪዎች ውጤት መሰረት
- በተመካሪነት የተሳተፉ ተማሪዎች በሀገር አቀፍ ፈተና 300 እና በላይ ባመጡት ውጤት መሰረት

# ክፍል ሶስት
# አደረጃጀት እና አመራር

**በከተማ ደረጃ**

1. ቢሮ ኃላፊ ----------------------------------------ሰብሳቢ
2. ም/ቢሮ ኃላፊ-------------------------------------ፀኃፊ
3. የሱፐርቪዢን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር-----አባል
4. የአማርኛ ስርዓተ ትምህርት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር-- አባል
5. የአፋን ኦሮሞ ስርዓተ ትምህርት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አባል
6. የፈተና ዝግጅት እና ምዘና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አባል
7. የወተማ አባል
8. የመምህራን ማህበር አባል

**በቢሮ ደረጃ የተዋቀረዉ አደረጃጀት ተግባርና ሀላፊነት**

- ፕሮግራሙን በበላይነት መምራት
- በስትራቴጂዉን ዙሪያ በከተማ ደረጃ የግናዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማካሄድ
- ለትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ለትምህርት አመራሮች፣ ለባለሙያዎች፣ ለሱፐርቫይዘሮች እና ለመምህራን የስራ መመሪያ መስጠት
- የመምህራን መመልመያ መስፈርት ማዘጋጀት እና ለክፍለ ከተማ ማውረድና አፈጻፀሙን መከታተል
- የትምህርቱን ይዘት በማዘጋጀት፤ ተደረሽ ማድረግና አግባብነቱን ማረጋገጥ
- በየክፍለ ከተማዉ ለተመረጡ መምህራን በከተማ ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት
- ስልጠናው እና ስትራቴጂው በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመራ ኃላፊነት መስጠት
- በክላስተር ደረጃ ማጠናከሪያ ለሚማሩ ተማሪዎች ስታንዳርዱን የጠበቀ፤ ለአገር አቀፍ ፈተና የሚያዘጋጅ ሞዴል ፈተና ማዘጋጀትእና ማስፈፀም
- ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ለተማሪዎች፤ ለመምህራን እንዲሁም ለተመረጡ ተማሪ ወላጆች/ አሳዳጊዎች የስነ ልቦና ማማከር ስርዓት መዘርጋት

- በየክፍለ ከተማዉ በክላስተር ማጠናከሪያነት የተመረጠዉ ትምህርት ቤት በመስፈርቱ መሆኑን ማረጋገጥ(ላጎራባች ትምህርት ቅርብ መሆናቸዉን፤የተማሪ ቁጥር ብዛት እና ግብዓት የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ
- በየወሩ በሁሉም የክላስተር ማዕከላት ድጋፍና ክትትል በማድረግ በአንድ ማዕከል ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ ግብረ መልስ የጋራ ማድረግ እና ያሉበትን ደረጃ በክፍለ ከተማ ፤ በክላስተር ፤ በትምህርት ቤት ደረጃ ፍረጃ ማካሄድ እና የተሻለ አፈፃፀም ያላቸዉን ክላስተር ተሞክሮ እንዲቀምሩ ማድረግ፡
- በየደረጃው ያሉ አካላት የተጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ፤
- በስትራቴጂዉ ትግበራ ላይ ዉጤታማ ለሆኑ ማለትም የተለዩትን ተማሪዎች 100% ያሳለፉ ክላስተር ማዕከላት እዉቅና መስጠት እና የተቀመጠዉን ግብ ያላሳኩ ተጠያቂ ማድረግ

## በክፍለ ከተማ ደረጃ

1. ትምህርት ፅ/ቤት ኃላፊ ---------------------------------------- ሰብሳቢ
2. የሁለቱም ዘርፍ አስተባበሪዎ---------------------------------------- ፀሀፊ
3. የ2ኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘር አስተባባሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች -----አባል
4. የአማርኛ ስርዓተ ትምህርት ቡድን አስተባባሪ ------------------- አባል
5. የአፋን ኦሮሞ ስርዓተ ትምህርት ቡድን አስተባባሪ ---------------አባል
6. የሁሉም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን---------- አባል
7. የወተማ --------------------------------------------------------------------አባል
8. የመምህራን ማህበር -----------------------------------------------------አባል

## በክፍለ ከተማ ደረጃ የተዋቀረዉ አደረጃጀት ተግባርና ሀላፊነት

- ደረጃውን የጠበቀ የቶፕ-25 ተማሪዎች ማጠናከሪያ ክላስተር ማዕከል ማዋቀር
- የተዋቀሩትን ክላስተር ማዕከላት በበላይነት መምራት
- በስትራቴጂዉ ዙሪያ በክፍለ ከተማ ደረጃ ለባለድርሻ አካላት (ሱፐርቫዘሮች፤ ለክፍለ ከተማ ባለሙያዎች ፤ርዕሳነ መምህርን ፤ ወተመ እና መምህራን ማህበር ) የግናዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት

- ከቢሮ በወረደዉ መስፈርቱ መሰረት መምህራንን አወዳድሮ በመለየት ለክላስተር ማዕከላት ተደራሽ ያደርጋል
- በክፍለ ከተማዉ ለተመረጡ መምህራን  የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ማዘጋጀት እንዲሁም የሚሰጡ ስልጠናዎች በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመሩ እና በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በከተማ ደረጃ ተዘጋጅቶ የመጣዉን  ሞዴል ፈተና ማስፈፀም
- ለተማሪዎች፣ ለመምህራን እንዲሁም ለተመረጡ ተማሪ ወላጆች/ አሳዳጊዎች የስነ ልቦና ምክር  የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ተፈፃሚ ማድረግ
- ከቢሮው በወረደው አቅጣጫ መሰርት ክላስተር ማከል ትምህርት ቤትን መርጦ ማዘጋጀት (ላጎራባች ትምህርት ቅርብ መሆናቸዉን፣የተማሪ ቁጥር ብዛት እና ግብዓት የተሟላ መሆኑን ማረጋገጥ/
-  በሁሉም የክላስተር ማዕከላት በየሳምንቱ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የአካል እና የፅሁፍ ግብረ መልስ መስጠት
- የተጠያቂነትና የጠያቂነት ስርዓት በመዘርጋት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ፤
- በክፍለ ከተማ ደረጃ በስትራቴጂዉ ትግበራ ላይ ዉጤታማ ለሆኑ ማለትም የተለዩትን ተማሪዎች 100% ያሳለፈ  ክላስተር ማዕከላት እና ት/ቤቶች  እዉቅና መስጠት እና የተቀመጠዉን ግብ ያላሳኩ ተጠያቂ ማድረግ

**በክላስተር ማዕከል  ደረጃ**

1. የክላስተሩ ዋና ር/መምህር --------------------------------- አስተባባሪ እና ሰብሳቢ
2. የተመረጠዉ ክላስተር ማዕከል ትምህርት ቤት ም/ር/መምህራን…አባል (እንደሚናቸው)
3. ክላስተር ማዕከል ስር ያሉ ሁሉም የመንግስት እና የግል ት/ቤቶች ዋና ር//ራን-- አባላት
4. የ2ኛ ደረጃ ሱፐርቫይዘር --------------------------------------------- የማዕከሉ ሱፐርቫይዘር
5. የተመረጠዉ ክላስተር ማዕከል ትምህርት ቤት አንድ ዩኒት መሪ ---------- አባል

**በክላስተር ደረጃ የተዋቀረዉ አደረጃጀት ተግባርና ሀላፊነት**

- የሁሉንም ትምህርት ቤቶች ቶፕ 25 ተማሪዎች መረጃ ማደራጀ
- ተማሪዎችን ከመንግስት እና ከግል የተወጣጡ በማድረግ ከፍል መደልደል እና ማሳወቅ
- የክላስተር ማዕከሉ ስርዓተ ትምህርት ምክትትል ርዕሰ መምህር የክፍለ ጊዜ ድልድል በስትራቴጂዉ በተቀመጠዉ መሰረት ይሰራል

- ለክላስተሩ የሚያስፈልጉ ግበዓቶችን መለየት እና እንዲሟላ ማድረግ
- በትምህርት ዓይነቱ እና በክፍል ደረጃ የትምህርት እቅድ (lesson plan) እየተዘጋጀ በስርዓተ ትምህርት ምክትል ርዕሰ መምህር እየተረጋገጠ ይሄዳል
- የሁሉም ትምህርት ቤቶች የግልና የመንግስት ዋና ር/መምህራን በተወሰነዉ መሰረት ለክላስተሩ በተማሪያቸዉ ቁጥር ልክ በተከፈተዉ አካዉንት ገንዘብ ገቢ ማድረግና ለሚመለከታቸዉ አካላት ክፍያ መፈፀም እና መረጃ ለሚመለከተዉ አካል መስጠት
- ከቢሮ በወረደዉ የትምህርት ይዘት መሰረት ትምህርቱ መሰጠቱን ማረጋገጥ
- እንደ ክላስተር በየትምህርት ዓይነቱ ወርክሽት እንዲዘጋጅ ማድረግ እንዲሁም ለቀጣይ ሳምንት ጥያቄዉን ሰርተዉ እንዲመጡ ማድረግ
- መጠይቅ በማዘጋጀት ተማሪዎች በየትምህርት አይነቱ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ካሉ እንዲሻሻሉ ማድረግ
- የክሊኒካልና የውስጥ ሱፐርቪዥን አገልግሎት የመጡ ለውጦችን ለመገምገም ያስችል ዘንድ የሱፐርቪዥን አገልግሎት ፋይዳ ዳሰሳ በየደረጃው ማካሄድ፣

**በት/ቤቶች ደረጃ**

1. ትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ---------------- ሰብሳቢ
2. የስ/ትምህርት ም/ር/መምህር -------------------- ፀሀፊ
3. የመምህራን ልማት ምክትል ር/መምህር -------- አባል
4. የትምህርት ቤት ምክትል ር/መምህር -------- አባል
5. የትምህርት ቤት ዩኒት መሪዎች ------------------------- አባላት
7. የወተማ ሰብሳቢ ----------------------------------------------- አባል
8. መሰረታዊ መምህራን ማህበር ሰብሳቢ --------------------------- አባል
9. የተማሪ ተወካይ (ከ11ወይምከ12ኛ ክፍ---------------------------------------- አባል

**<u>በትምህርት ቤት ደረጃ የተዋቀረዉ አደረጃጀት ተግባርና ሀላፊነት</u>**

**<u>የር/መምህርን ተግባር</u>**

- ስትራቴጂውን በተመለከተ በወረደዉ የድርጊት መረሀ ግብር መሰረት ግብዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ
- እንደ ትምህርት ቤቱ ነባራዊ ሁኔታ ስትራቴጂዉን ዉጤታማ የሚያደርጉ ዉስጣዊ አሰራሮችን ይዘረጋል

- በትምህርት ቤቱ የሚሰጡ ስትራቴጂዎቹን ትግበራ ስረዓት መዘርጋት ፤መከታተል መደገፍ እና ግብረ መልስ መስጠት
- ተማሪዎች በስትራቴጂዎቹ ተገኝተዉ እንዲማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ የተገኙ እና ያልተገኙ ተማሪዎች መረጃ ወስዶ ያደራጃል ፤የቀሩ ተማሪዎች ለይቶ ከወላጆቻቸዉ ጋር ዉይይት ያደርጋል
- ስትራቴጂውን መሰረት ያደረገ ለም/ር/መምህራን ስራ ያከፋፍላል ይመራቸዋል
- በክላስተር ማዕከል የሚሰጠውን ኃላፊነት ሙሉ ለሙሉ ይወጣል

<u>**የስርዓተ ትምህርት ምክትትል ር/መምህር**</u>

- ከመደበኛ ክፍለ ጊዜ በፊት/ Before Class/ እና የቅዳሜ የማጠናከሪያ ትምህርትን በሃላፊነት ይመራል
- ተማሪዎችን ከመደበኛ ክፍለ ጊዜ በፊት ለሚሰጠዉ የማጠናከርያ ትምህርት ከ1-25 የወጡትን እና ቀሪዎችን ለይቶ ክፍል ይመድባል
- በስትራቴጂዉ በተቀመጠዉ መሰረት የጠዋት ማጠናከሪያ ሰኞ፤ እሮብ አርብ ለሚሰጡ መምህራን ፕሮግራም ያወጣል ተፈፃሚነቱን ይከታተላል
- ተማሪዎች ጠዋት 1፤00 ሰዓት ተገኝተዉ እንዲማሩ ግንዛቤ ይፈጥራል፤የተገኙ እና ያልተገኙ ተማሪዎች ይለያል ፤የቀሩ ተማሪዎችን ለይቶ የክፍል ሀላፊ መምህራን ምክኒያታቸዉን ጠይቀዉ ፕሮግራሙን እንዲቀላቀል ያደርጋል
- የተለያዩ ጥያቄዎች(ወርክ ሽቶች)፤ ስልቶች፤ ፈተናዎች እንዲዘጋጁ ማድረግ
- መምህራን ያስተማሯቸውን ተማሪዎች ውጤት ትንተና (የማሳለፍ ምጣኔ) እንዲያደራጁ ማድረግ
- ስትራቴጂዎቹን መሰረት ያደረጉ የመማር ማስተማር ር/መ/ር ስራዎችን ይፈፅማል ያስፈፅማል

<u>**የመምህራን ልማት ምክትል ር/መምህራን**</u>

- ተማሪዎችን የማማከር ስትራቴጂ በዋናነት ይመራል
- አንድ መምህር ከ5-7 የሚሆኑ ተማሪዎችን ይዞ እንዲያማክር ያደራጃል ፤የማማከሪያ ሰዓት ይወስናል ተፈፀሚነቱን ይከታተላል
- የ11ኛ እና 12 ክፍል መምህራን ፕሮፋይል በተማሪዎቻቸው የፈተና ውጤት መሰረት ያደረገ ያደራጃል
- የተመረጡ መምህራንን ከስርዓተ ትምህርት ጋር በጋራ በመሆን ይደለድላል

- ቼክሊስት በማዘጋጀት ተማሪዎች ስለ ሚሰጣቸዉ የማማከር አገልግሎት አስተያየት ይቀበላል መሻሻል ያለበትን እንዲሻሻል ያደርጋል
- በሁሉም ስትራቴጂዎች የመምህር አመራር ኃላፊነቱን በብቃት ይወጣል
- ስትራቴጂዎቹን መሰረት ያደረጉ የመምህራን ልማት ም/ር/መ/ር ስራዎችን ይፈፅማል ያስፈፅማል

## የትምህርት ቤት መሻሻል ም/ር መምህር

- በዋናነት የጥናት ፎረሙን ይመራል
- የጥናት ፎረሙ የሚካሄድበትን ቦታ ያመቻቻል
- በዉጤታቸዉ የተለዩ ተማሪዎችን  ቅጽ በማዘጋጀት አንድ ጎበዝ ተማሪ በስሩ አምስት (5) ተማሪዎችን እንዲይዝ አድርጎ  ያደራጃል
- በፕሮግራሙ መሰረት ማክሰኞ እና ሀሙስ የሚደረገዉን የትናት ፎረም የሚከታተል መምህር መድቦ ያሳዉቃል ፤የተገኙ እና ያልተገኙ መምህራንን ይለያል
- በተቀመጠዉ የግዜ ሰሌዳ መሰረት ሁሉም ተማሪዎች በጥናት ፎረም በአቴንዳስ ይከታተላል
- ቼክሊስት በማዘጋጀት ዉጤታማነቱን  ይከታተል መሻሻል ያለበትን እንዲሻሻል ያደርጋል
- ስትራቴጂዎቹን መሰረት ያደረጉ የት/ቤት መሻሻል ም/ር/መ/ር ስራዎችን ይፈፅማል ያስፈፅማል

## የአማካሪ መምህራን ተግባርና ሀላፊናት

- በተመካሪነት የተመደቡለትን ተማሪዎች የመማር ብቃትና ተነሳሽነት ይለያል
- ተማሪዎች በእቅድ እንዲመሩ፤ግዜያቸዉን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደርጋል
- ተማሪዎችን ለአገር አቀፍ ፈተና ዝግጁ የሚያደርግ አነቃቂ ምክር ይሰጣል
- ተማሪዎች የስነ ልቦና ተነሳሽነታቸዉ እንዲጨምር ያማክራል
- ከወላጆች ጋር በጋራ በመስራት ልጆቻቸዉን እንዲከታተሉ ያደርጋል
- ልምዱን እና ሙያዊ እዉቀቱን ማስተላለፍ
- ከመማር አንፃር የሚገጥማቸዉን ችግር መፈታት እንዲችሉ ማብቃት
- የተማሪዎችን እዉቀት እና ክህሎት የሚገነቡበት ዉጤታማ የሆነ የጥናት ስነ ዘዴ ያስገነዝባል
- የፈተና ዉጤታቸዉን ይከታተላል

## የዩኒት መሪ ተግባር እና ሃላፊነት

- ተጠሪነቱ ለምክትል ርዕሳና መምህራን ሆኖ ስትራቴጂዉ ዉጤታማ እንዲሆን በተሰጠዉ ተግባና ሃላፊነት መሰረተ ይደግፍል፤ይከታተላል
- በትምህርት ቤት የሚካሄደዉን የጠዋት ፤ቅዳሜ እና የጥናት ፎረም በአግባቡ መካሄዱን ይከታተላል
- የሚያረፍዱ፣ የሚቀሩና ስነምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን ይቆጣጠራል፣
- በስትራቴጂዉ በላይ ያረፈዱና የቀሩ እንዲሁም የስነምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ወላጆች በመጥራት ያነጋግራል፣
- ቶፕ 25 እና ሌሎች የክፍል ውስጥ አደረጃጀቶችን በመጠቀም የተማሪዎች መማር ማስተማሩንና ስነምግባርን ይቆጣጠራል፣
- በትምህርት ቤቱ አመራር የሚሰጠው ተጨማሪ ስራዎች ይሰራል፤ ይተገብራል፣

## በስትራጂው ትግበራ የክፍል ሀላፊ ትግባርና ሀላፊነት

- ተጠሪነቱ ለምክትል ርዕሰ መምህራን ሆኖ የተመደበበትን ክፍል ተማሪዎች ሙሉ መረጃ ይይዛል፤የተማሪዎች ስም ይጠራል፣ ቀሪ ተማሪዎችን ወላጅ በማስጠራት በፕሮግራሙ እንዲሳተፉ ያደርጋል
- ስም ለሚጠራበት ክፍል በስትራቴጂዉ ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል
- ተማሪዎች ያቀዱትን እቅድ እንዲያሳኩ ያግዛል
- የሚያረፍዱ፣ የሚቀሩና ስነምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን ይቆጣጠራል፣
- በክፍሉ ተማሪዎች ውጤትና ትምህርት አቀባበል ዙሪያ ከወላጆች ጋር ይወያያል፣
- ቶፕ-25 እና ሌሎች የክፍል ውስጥ አደረጃጀቶችን በመጠቀም የተማሪዎች መማር ማስተማሩንና ስነምግባርን ይቆጣጠራል፣
- በተመደበበት ክፍል ዉስጥ የስትቴጂዉን ውጤታማነት ይከታተላል፤ ይገመግማል መሻሻል የሚገባቸዉን እንዲሻሻል የመፍትሄ ሃሳብ እና ስልት ያቀርባል

# የስትራቴጂው ማስፈፀሚያ የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ/ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | ተግባራቱ የሚከናወኑበት ወራቶች | | | | | | | | ፈፃሚ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መስከ | ጥቅ | ህዳ | ታህ | ጥር | የካ | መጋ | ሚያ | |
| 1 | እቅድ ማዘጋጀት | ✓ | | | | | | | | |
| 2 | የተዘጋጀ እቅድ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ማፀደቅ | ✓ | | | | | | | | |
| 3 | ከከተማ እስከ ክፍለ ከተማ ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት ኦረንቴሽን መስጠት | ✓ | | | | | | | | |
| 4 | በትምህርት ቤቶች ለመምህራን ኦረንቴሽን መስጠት | ✓ | | | | | | | | |
| 5 | መምህራንን መለየት እና ኦረንቴሽን መስጠት | ✓ | | | | | | | | |
| 6 | ሀብት ማሰባሰቢያ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት እና ማፀደቅ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 7 | ሀብት የማሰባሰብ ስራ መስራት | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 8 | መማር ማስተማሩን ማካሄድ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 9 | የተሻለ ውጤት ያላቸው ተማሪዎችን መሸለም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 10 | የመማር ማስተማሩ ያለበትን ደረጃ መገምገም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |
| 11 | ለመምህራን እና የተለያዩ ክፍያዎችን መፈፀም | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | |

# ማጠቃለያ

ትምህርት ለሀገር ሁለንተናዊ እድገት ያለውን ሚና በመገንዘብ በአስተሳሰብ እና በክህሎት የዳበር ትውልድ ለመገንባት በአጠቃላይ ትምህርቱ የሚከናወኑ ጥራት ማስጠበቂያ ስልቶች ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ስለሆነም በባለፈት አራት ተከታታይ አመታት የ12ኛ ክፍል አአገር አቀፍ ፈተና አገር ተረካቢ ዜጎች ያሉበትን የዝግጅት ሁኔታ የሚያሳይ እንደመሆኑ በዘርፉ በልዩ ትኩረት መስራት አስፈላጊ መሆኑን ያመላከተ ነው፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በመደበኛ መማር ማስተማሩ ባሻገር የትምህርቱ ማህበረሰብ ያለውን ብቃት ሁሉ አሟጦ የሚጠቀምበት ሞዳሊቲ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ብቃት ያላቸው መምህራን እና የትምህርት አመራሮች በልዩ ትኩረት የሚፈፅሙ ወላጆች በፋይናንስ የሚሳተፉበት፣ በበአአንድ አካባቢ ያሉ የግል እና የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች በጋራ የሚማማሩበት የክላስተር ጥናት ማዕከል መተግበር የሚያስችል እቅድ አዘጋጅተናል፡፡ ስለሆነም የተመላከቱት የትምህርት ማህበረሰብ አካላት በዘርፉ በሚያደርጉት አስተዋፅኦ የ12ኛ ክፍል አሀገር አቀፍ የተማሪዎች ውጤት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚሻሻል ባለሙሉ እምነት ነን፡፡

## አባሪዎች

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ "የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ማሻሻያ ስትራቴጂ"ን**

**በት/ቤት ደረጃ ለመተግበር የተዘጋጀ መርሃ ግብር**

A. የሁሉም ስትራቴጂዎች ሳምንታዊ የግዜ ሰሌዳ

| | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ከ1፡00-2፡00 | B-class<br>$B_1$ School based<br>$B_2$ Top-25 | | B-class<br>$B_1$ School based<br>$B_2$ Top-25 | | B-class<br>$B_1$ School based<br>$B_2$ Top-25 | | |
| ከ2፡30-6፡30 | | | | | | Cluster tutor<br>School based | |
| ከ7፡30-9፡00 | | | | | | Cluster tutor<br>School based | |
| ከ9፡30-12፡00 | | A-class<br>Study forum | | A-class<br>Study forum | | | |

B. የትምህርት ዓይነት የክፍለ ጊዜ ምጣኔ

| ተ.ቁ | የትምህርት ዓይነት | CODE | A-class (9፡30-12፡00) | $B_1$-class (1፡00-2፡15) | $B_2$-class (1፡00-2፡15) | Cluster (2፡30-9፡30) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Math | M | 1 | 2 | 1 | 1፡30 |
| 2 | English | E | 1 | 1 | 1 | 130 |
| 3 | Chemistry/ Geography | CG | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 4 | Physics/ History | PH | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 5 | Biology/ Economics | BE | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 6 | SAT | S | | | | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | 5 | 6 | 6 | 6 |

## C. ሳምንታዊ መርሃ ግብር

| | 1ኛ ሳምንት | | | | | | | | 2ኛ ሳምንት | | | | | | | | 3ኛ ሳምንት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ | | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ | | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ | ቅዳሜ | እሁድ | |
| 1፡00-2፡30 | PH | | CG | | E | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | M | CG | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 2፡30-6፡30 | | | | | | BE | S | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 7፡30-9፡00 | | | | | | E | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 9፡30-11፡30 | | M | | PH | | | | | | E | | CG | | | | | | BH | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |

የ2ኛ ደረጃ ዉጤት ማሳቂያ እስትራቴጂ ማስፈፀሚያ መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | ዋና ተግባር | የሚከናወኑ ተግባራት | የሚተገበርበት ጊዜ | የሚተገብር አካል |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስትራቴጂ ዝግጅት | 0 ንድፍ | | ኮሚቴ |
| 2 | | 1ኛ ደረጃ ንድፍ | | ኮሚቴ |
| 3 | | የተጠናቀቀ | | ኮሚቴ |
| 4 | ውይይት (ስትራቴጂውን ማስተዋወቅ) | ቢሮ | ሐሙስ 06/02/2017 | ትምህርት ቢሮ |
| 5 | | ለክፍለ ከተማ ጽ/ቤት ሃላፊዎች | ሐሙስ 06/02/2017 | ትምህርት ቢሮ |
| | | ለር/መምህራን | ሐሙስ 06/02/2017 | ትምህርት ቢሮ |
| 6 | | ለመምህራን | | ትምህርት ቢሮ |
| 7 | | ለር/መምህራን | ዓርብ 07/02/2017 | ክ/ከተማ |
| 8 | | ለመምህራን | ዓርብ 07/02/2017 | ክ/ከተማ |
| 8 | | ለወላጆች | ቅዳሜ 08/02/2017 | ክ/ከተማ |
| 9 | | | | |
| 10 | | ከመምህራን | ቅዳሜ 08/02/2017 | ት/ቤት |
| 11 | | ከተማሪ | ቅዳሜ 08/02/2017 | ት/ቤት |
| | | ከወላጆች | ቅዳሜ 08/02/2017 | ት/ቤት |
| | | | | |
| | ስትራቴጂውን ማስጀመር | በት/ቤት | ሰኞ 10/02/2018ዓ.ም | በት/ቤት |
| | | በክላስተር | ቅዳሜ | ክላስተር ማዕከል |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |